NØDVARSEL

# የአደጋ ጊዜ ማንቂያ በሞባይል ስልክ

## ማስጠንቀቂያውን ያንብቡ፣ ምን ማድረግ እንዳለቦት ይወቁ።

ከባድ አደጋዎች በድንገት ሊከሰቱ ይችላሉ። ምን አይነት ከባድ አደጋ እየተከሰተ እንዳለ እና ምን ማድረግ እንዳለቦት መረጃን በፍጥነት ማግኘት አስፈላጊ ነው። የአደጋ ጊዜ ማንቂያ መልክት ሊደርሶት ይችላል። ይህ ማለት እርስዎ ባሉበት ቦታ ላይ ከባድ የህይወት እና የጤና አደጋ ከተከሰተ በሞባይል ስልክዎ ላይ ጠቃሚ መረጃ ያለው የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ሊደርስዎት ይችላል።

የአደጋ ጊዜ ማንቂያው **ምን እየተከሰተ እንዳለ እና ምን ማድረግ እንዳለቦት** የሚገልጽ አጭር ጽሑፍ ይይዛል። የእርስዎን ትኩረት ለማግኘት ስልኩ ይንቀጠቀጣል እና ጮክ ያለ ሳይረን የመሰለ ድምጽ ይሰማል። የአደጋ ጊዜ ማሳወቂያ መልክት ሲደርስዎ መልክቱን ማንበብ እና ምን ማድረግ እንዳለቦት መልክቱን መከተል አለብዎት።

## ከመንግስት የሚሰጥ አገልግሎት

የአደጋ ጊዜ ማንቂያ አገልግሎት ከኖርዌይ መንግስት የሚሰጥ አገልግሎት ነው። እንደዚህ አይነት ማንቂያዎችን ሊያወጣ የሚችለው ፖሊስ ወይም የኖርዌይ ሲቪል መከላከያ ብቻ ነው።

በርካታ የአውሮፓ ሀገራት ይህንን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ዜጎቻቸውን እንደ ጎርፍ፣ የሽብር ጥቃቶች እና የኬሚካል ልቀቶች ካሉ ከባድ አደጋዎች ህዝባቸውን ለማስጠንቀቅ ጥሩ ልምድ አላቸው። በኖርዌይ ውስጥ በሞባይል ስልኮች ላይ የሚላኩ የአደጋ ጊዜ ማንቂያዎች ከህይወት እና ጤና አደጋ ሊያድኑ ይችላሉ።

የሞባይል ስልክ የአደጋ ጊዜ ማንቂያ ህዝቡን አደጋ እንዳለ ለማሳወቅ ጥቅም ላይ ከሚውሉ መንገዶች ተጨማሪ መንገድ ነው። በኖርዌይ ውስጥ ለረጅም ዘመናት አደጋ ሲደርስ ለህብረተሰቡ ታላቅ ድምፅ በሚያወጡ ጡሩንባዎች አማካኝነት ማንቂያ መልክትቶች ይሰጣሉ። ከባድ አደጋ በሚፈጠርበት ጊዜ ጠቃሚ መረጃዎች እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ድረ ገፅ ጋዜጦች፣ በመንግስት ድረ ገጾች እና በማህበራዊ ሚዲያዎች ላይ ይሰራጫሉ።

ታላቅ ድምፅ የሚያወጡ ጡሩንባዎች በየስድስት ወሩ መስራታቸው እንደሚሞከር ሁሉ በሞባይል ላይ ያለው የአደጋ ጊዜ ማንቂያ በየተወሰነ ጊዜ መስራቱ መሞከር አለበት።

## በሞባይል ላይ የአደጋ ጊዜ ማንቂያው የሚሰራው በሚከተለው መንገድ ነው

የድንገተኛ ጊዜ ማንቂያ በተንቀሳቃሽ ስልክ ኔትወርክ በኩል በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ እንደዚህ አይነት መልዕክቶችን መቀበል ለሚችሉ ሁሉም የሞባይል ስልኮች ይላካል። በመልክቱ ውስጥ ያለው ጽሑፍ በኖርዌጂያን ወይም በእንግሊዝኛ ይሆናል፣ ይህም ስልክዎ ላይ በየትኛው ቋንቋ እንደሚጠቀሙ ይወሰናል። ስልክዎ ጽሁፍን ወደ ንግግር የሚቀይር ከሆነ መልክቱን ጮክ ብሎ እንዲያነብ ማድረግ ይችላሉ።

የአደጋ ጊዜ ማንቂያ መልክት የስልክ ቁጥርዎን ወይም ስለእርስዎ ወይም ስለስልክዎ ሌላ መረጃ አይጠቀምም። የአደጋ ጊዜ ማንቂያዎችን ለመቀበል መመዝገብ ወይም መተግበሪያ ስልኮ ላይ መጫን አያስፈልግዎትም። ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው። ማስታወስ ያለብዎት ነገር ስልክዎን አዲስ ሶፍትዌር ሲኖር ማዘመን (አፕዴት ማድረግ) ነው።

በተጨማሪም በድረገፅ emergencyalert.no ላይ የበለጠ ያንብቡ።

POLITIET

dsb Direktoratet for samfunnssikkerhet og beredskap

SIVILFORSVARET